# የቤተሰብ-አስተማሪ አጋርነትን መገንባት

ቶኪንግ ፖይንትስ/TalkingPoints ለሚጠቀሙ ቤተሰቦች የተሻሉ አሰራሮች

ከልጅዎ አስተማሪዎች ጋር ውጤታማ ግንኙነት ማድረግ ትምህርታቸውን ለመደገፍ እና አወንታዊ የመማሪያ አካባቢን ለማሳደግ ወሳኝ ነው። ከልጅዎ አስተማሪዎች ጋር ትርጉም ባለው እና ገንቢ በሆነ መልኩ እንዲሳተፉ ለማገዝ፤ ከምሳሌዎች ጋር የቀረቡ አምስት ምርጥ ተሞክሮዎች እዚህ ይገኛሉ።

### በቅድሚያ ግንኙነት ይፍጠሩ

እራስዎን ለማስተዋወቅ እና የግንኙነት ምርጫዎን ለማሳወቅ፤ በትምህርት አመቱ መጀመሪያ ላይ የልጅዎን አስተማሪዎች ያግኙ። የልጅዎን ትምህርት ለመደገፍ ቁርጠኛ መሆንዎን ያሳውቋቸው። ለምሳሌ በዚህ መልዕክት መጀመር ይችላሉ፡- “ሰላም (የአስተማሪ ስም)፣ እኔ (የእርስዎ ስም) እባላለሁ፤ (የተማሪ ስም) ወላጅ ነኝ፣ እኔ ራሴን ለማስተዋወቅ እና በትምህርት አመቱ ሙሉ (የተማሪ ስም)ን ለመደገፍ ያለኝን ጉጉት መግለጽ ፈልጌ ነው። " በእንግሊዝኛ=("Hello (Teacher's Name), I am (Your Name), (Student's Name)'s parent. I wanted to introduce myself and express my eagerness to support (Student's Name) throughout the school year.")

### አዎንታዊ እና ክብር የሚሰጡ ይሁኑ

በሁሉም የመልዕክት ልውውጥዎ ውስጥ አዎንታዊ ቃና ይኑርዎት እንዲሁም አክባሪ ይሁኑ። ከአስተማሪዎች ጋር ጥሩ ግንኙነት የሚገነባው በጋራ መከባበር እና መግባባት ላይ ነው። ለምሳሌ፣ መልእክት በሚከተለው መጀመር ይችላሉ "ከ(የተማሪ ስም) ጋር ለሚሰሩት ጠንካራ ስራ ሁሉ አመሰግንዎታለሁ። ትምህርታቸውን ለመደገፍ የሚያደርጉትን ሁሉ አደንቃለሁ"

### በዝርዝር ያሳውቁ

ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ሲኖሩዎት ስለ ጉዳዮቹ ግልጽ ይሁኑ። አስተማሪዎች ስጋቶችዎን በተሻለ ሁኔታ ተረድተው መፍትሄ እንዲሰጡ፤ ዝርዝር መረጃ መስጠት ይጠቅማል። ለምሳሌ፡- “ይህን አስተውያለሁ፤(የተማሪ ስም) በቅርብ ጊዜ የሂሳብ የቤት ስራቸውን መስራት እየቸገረው/ራት ነው። አንዳንድ ተጨማሪ መገልገያ ግብዓቶችን መስጠት ይችላሉ ወይም በቤት ውስጥ እንዲሻሻሉ መርጃዎችን ወይም መንገዶችን መጠቆም ይችላሉ?

### ጠቃሚ መረጃ ያጋሩ

በልጅዎ ህይወት ውስጥ ስላሉ ማናቸውም ጉልህ ለውጦች ወይም ክስተቶች በትምህርት ቤት ባህሪያቸው ወይም አፈጻጸም ላይ ተጽእኖ ስለሚያሳድሩ ለአስተማሪዎች ያሳውቋቸው። ይህ መረጃ መምህራን የተሻለ ድጋፍ እንዲሰጡ ይረዳል። እንደዚህ ባለ መልእክት ሊጀምሩ ይችላሉ: "(የተማሪ ስም) በቤት ውስጥ ትልቅ ለውጥ እንዳለ እና በክፍል ውስጥ ትኩረታቸውን ሊጎዳው እንደሚችል ላሳውቅዎ ፈልጌ ነበር ። እባክዎን ይከታተሉ እና ማናቸውም ጉዳዮችን ካስተዋሉ ያሳውቁኝ ።"

### ተከታይ መልዕክት ይላኩ

ስለ አንድ ስጋት ወይም ጉዳይ ከአንድ አስተማሪ ጋር ከተነጋገሩ በኋላ፤ ነገሮች እንዴት እየሄዱ እንደሆነ ለማወቅ በተከታይ ያግኟቸው። ይህ እርስዎ እንደተሳተፉ ያሳያል እንዲሁም ማንኛውም ስምምነት የተደረገባቸው ድርጊቶች መተግበራቸውን ለማረጋገጥ ይረዳል። ተከታዩን መልእክት በሚከተለው መጀመር ይችላሉ “ሰላም (የአስተማሪ ስም)፣ ባለፈው ሳምንት በተነጋገርነው ጉዳይ ላይ (የተማሪ ስም) ያላቸውን ለውጥ ለመረዳት ፈልጌ ነበር የማገኝዎ። መሻሻሎች ወይም ለውጦች አስተውለዋል?”